# ከራስ ጋር መታረቅ

አዲሱ የኢትዮጵያ ጠ/ሚር አብይ አህመድ በሀገር ቤትም ሆነ በዲያስፖራው እንዳየነው ከፍተኛ የሆነ ድጋፍ ያገኙ ይመስላል ። እውን ይህ ድጋፍ ዘለቄታዊነት ይኖረው ይሆን? የራሴን ጥያቄ እራሴው ልመልሰውና "ጊዜ ይፍታው እላለሁ" ።

በርግጥ ባለፉት 27 ዓመታት ወያኔ በኢትዮጵያ ላይ ባደረሰው ገደብ የለሽ ጭቆና ፣ ግድያ ፣ እስር ፣ ዘረፋ ፣ አገር ማፈራረስ ወዘተ … ባዕዳዊ ተልዕኮውን የኢትዮጵያን ህዝብ እጅግ ስላስመረረው አሁን የመጣውን የጠ/ሚር አብይ አህመድ አስተዳደር በደንብ ሳያጤንና ሳያላምጥ ጥላቻው ስላሸነፈው ብቻ በግርድፉ እየዋጠ እንዳለ ህሊና ያለው ለማስተዋል ይቸገራል ብዬ አልገምትም ።

የኛ ትልቁ ችግራችን በአንድ ስርአት ስንከፋ ማንም ይምጣ ማን ጥላቻችን ስለሚያሸንፈን የመጣውን ሆ! ብሎ መቀበል እንወዳለን ፣ ይህ ክፉኛ የተጠናወተን ተፈጥሮአችን ከኃይለ ስላሴ ወደ ደርግ ፣ ከደርግ ወደ ወያኔ አሁን ደግሞ ከወያኔ ወደ ኦሆዴድ ሲያሻግረን በተመሳሳይ ሁኔታ መከናወኑ እጅግ አሳዛኝ አካሄድ ቢባል ማጋነን አይሆንም ። አንድ ሊሰመርበት የሚገባ ነገር ቢኖር አሁንም በቅርቡ የተገኙ ድሎችን ያስገኘው የጠ/ሚሩ መልካም ፈቃድ ወይንም ትግል ሳይሆን ፣ በመላው ሀገሪቱ ህዝቡ ባደረገው የሞትና የሽረት ህዝባዊ እመጽ ነው . … በተደረገ ህዝባዊ አመፅ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል ። የህሊና እስረኞችም ፍቺም የህዝባዊው ትግል ውጠት እንጂ የጠ/ሚሩ ተጋድሎ እንዳልሆነ የማያውቅ ካለ ሊያውቀው የግድ ይላል ። ለዚህም ነው ዛሬም ህዝባዊው ትግል ተጠናክሮ መቀጠል አለበት የሚባለው ። ዛሬም በሺዎች የሚቆጠሩ የህሊና እስረኞች በመላው ሀገሪቱ ውስጥ እንደሚገኙ ይታወቃል ፣ ይህ ብቻ ሳይሆን ለበርካታ አመታት መዳረሻቸው ያልታወቀ አሁንም ብዙ ዜጎቻችን ስላሉ ዛሬም ትግሉ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የግድ ይላል ።

አዲሱ ጠ/ሚር በተደጋጋሚ ፍቅር ፣ ይቅርታ እያሉ ሲሰብኩ ሰምተናል ፣ ስለ ፍቅርና ይቅርታ ያላቸውን አመለካከት ሙሉውን መቀበል ቢያዳግተኝም ሆኖም ግን ይቅርታና ፍቅር ተገቢ መሆኑን አምናለሁ ፣ ነገር ግን ይህ በንዲህ እንዳለ ይቅርታ ለገደለ ፣ ላስገደለ ፣ አካል ላጎደለ ፣ ጥፍር ለነቀለ ፣ እግር ለቆረጠ ፣ ብልት ላኮላሸ ፣ ያገር እና የደሃ ሃብት ለዘረፈ ሁሉ ግፍና በደሉ ሳይቆጠር ለሰራው በደል ምንም አይነት ተጠያቂነት ሳይኖር እንዲያው በደፈናው ይቅር ተብሎ ከህዝብ ተቀቅፎ ይኑር ከሆነ ይህ ይቅርታን ሳይሆን የሚያስተምረው ፍርደ ገምድልነትን ስለሆነ ይህን አይነት አካሄድ ለመቀበል መለኮታዊ ጸጋን መላበስን ስለሚጠይቅ በሰውኛ ሊፈጸም ስለማይቻል የዚህ አይነት ይቅርታና ፍቅር ለመቀበል እጅግ ያዳግተኛል ፣ የወንድሜን ገዳይ ፣ ያባቴን ገዳይ ወዘተ … አግባብነት ያለውና ተመጣጣኝ የሆነ ፍትህ ሳይሰጥ መደመር በሚል አዲስ መዝሙር ብቻ ሊሰረዝና ሊደለዝ ስለማይቻል ይቅርታውና ፍቅሩ ተቀባይነት ያገኛል የሚል እምነት የለኝም ።

በሌላ አነጋገር ጠ/ሚሩ የኔን ድጋፍ ለማግኘት ከቃላት ባለፈ በተግባር ህዝባዊ የሆኑ ተግባራትን ሲያከናውኑ ማየት እፈልጋለሁ ። አዎ ብዙዎች የአስመራውን ግንኙነት እንደ ትልቅ ክንዋኔ ያዩት ይሆናል እኔ ግን አስመራን እንደ አንድ ሉአላዊ ሀገር ብቀበልም ጠ/ሚሩ የሰሩት ስራ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚያምነውንና የሚቀበለውን የአሰብን ወደብ ባለመብትነት ላንዴም ለሁሌም የመቃብር ሚስማራቸውን መተውበት እንደመጡ ነው የተሰማኝ ። ጠ/ሚሩ የሰሩት አሰብን በይገባኛል ዳግም እንዳናነሳ በአስመራ ፈቃድ በኪራይ ተጠቃሚ እንድንሆን ሲሆን ይህ ተግባራቸው አኩሪ ተግባር ሳይሆን አንገት ሊያስደፉን በተገባ ነበር ። ይህንን የዘመኑ የረቀቀ አሻጥር እለዋለሁ እንጂ ንብረቴን እንድከራይ ስላደረጉኝ በጭራሽ ላሞግሳቸው አልችልም ፣ አይገባኝምም ።

አሁንም ወደ ህሊናችን ብንመለስ ጠ/ሚሩ ያደረጉት በህዝብ የተጠሉና ህዝብን የበደሉትን በዙሪያቸው ከማሰባሰብ አልፎ ትላልቅ ሹመቶችን ሲሾሟዋቸው እንጂ አካባቢያቸውን ሲያፀዱና አዳዲስ ሰዎችን በችሎታና በዕውቀታቸው ሲያደላድሉ አላየንም ፣ አሁንም አልሸሹም ዞር አሉ ነው ። ሲቀጥልም ወያኔ ኢህደግ እንኳን በፓርላማው 2.5 ሚሊዮን አማራ ተነነ ፣ የት እንደገባ አላውቅም ያለውን በአማራው ላይ (Genocide)የዘር ማጥፋት ወንጀል አልተፈፀመም አልተካሄደም ብለው አይናቸውን በጨውው ታጥበው መልሰውልናል ። እና ጥያቀእው አማራውን ማን በላው? በወለጋ ፣ በጅማ ፣ በሲዳሞ ፣ በቤንሻጉል ወዘተ … ኧረ እስቲ አመራውን ያላፈናቀለ ፣ ያላሳደደ ፣ ያልገደለ በአራቱም ማዕዘን በኢትዮጵያ ውስጥ ብሄር በለው ብሄረሰብ አለ እንዴ? አናሳ ከሚባለው እስከ ትልቁ ብሄር ? ወይንስ ዋሾ እያሉን ይሆን ክቡር ጠ/ሚሩ?

ዶክተሩ በተደጋጋሚ ስለ ፍቅር ፣ እርቅና መደመር ሲሰብኩን ሁሌም የሚነግሩን መጀመሪያ "ከራስ ጋር መታረቅ" ነው ይላሉ ፣ እሺ ይሁን እኛ ከራሳችን ጋር የተጣላን ነን እርሳቸው ግን ከራሳቸው ጋር ታርቀዋል? ከሆነ በኔ አመለካከት ከራስ ጋር ለመታረቅ መጀመሪያ የሰሩትን ስህተት አምኖ መቀበልንና ህዝብን በሰሩት ስህተት ተፀፅቶ ይቅርታ መጠየቅን ስለሚያካትት ጠ/ሚሩን ከራስዎ ጋር መታረቅዎትን መጀመሪያ ለህዝብ አርአያ ሆነው እንዲያሳዩን ስለምንፈልግ የሚከተሉትን ስህተትዎን ተቀብለው በህዝብ ፊት ይቅርታን ሊጠይቁ ይገባል እላለሁ ።

፩) ተስፋዬ ገ/አብ በተባለ ኤርትራዊ የተፃፈን ተረት ተረት ትግባራዊ እንዲሆን ለአኖሌ ሃውልት ማሰሪያ የገንዘብ አሰባሳቢ መሆንዎ ትክክል እንዳልነበረ ።

፪) የአኖሌን ሃውልት ለማስመረቅ በስፍራው መገኘትዎ ትክክል እንዳልነበረ ።

፫) አሁን ደግሞ በተግባር በስልጣንዎ የአኖሌን ሃውልት በማፍረስ የህዝብ ወገን መሆንዎትን ማስመስከር ።

፬) አሁን የሚመሩት የኢትዮጵያን "ህዝብ" እንጂ ህዝቦች እንዳልሆነ ተገንዝበው በንግግርዎ ከወያኔ የወረሱትን የአፍራሽና ከፋፋይ አባባል "ህዝቦች" የሚለውን ቃል ካፍዎ በማስወገድ ህዝባዊነትዎን ማስመስከር ፣ ይውጋሽ ብሎ ይማርሽ ለርስዎም ሆነ ለማንም አይጠቅምምና ።

፭) በዲሲውም ስብሰባ ከጋዜጠኛ ቴዎድሮስ ፀጋዬ የተጠየቁትን ጥያቄ መልስ በመንፈግ በርግጥም ህዝባዊ ወገንተኝነትዎትን ማስመስከር ስላልቻሉ ለጥያቄው አፋጣን መልስ በመስጠት ከራስዎ ጋር ታርቀው ለሚመሩት ህዝብም አርአያ ሆነው ያሳዩን እላለሁ ።

ታዛቢው

July 30, 2018